# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 83 ታህሳስ 8 2002 ዓ.ም

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

አምባገነኖች ሰላም ማለት ሁሉም ሰው ከገዢዎች ተቆንጥሮ የሚሰጠውን መብት አመስግኖ ተቀብሎ፤ እንዲጫወት የታዘዘውን ባህርይ እየተጫወተ መኖር ማለት አድርገን እንድንወስድ ይፈልጋሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሰላም፣ ነፃነትና ክብር የማይነጣጠሉ ነገሮች መሆናቸውን ነው። ስለ ሰላም ማሰብ የምንፈልገው ሙሉ ስብዕናችን በተረጋገጠበት ሁኔታ እንጂ ስብዕናችን በተዋረደበት ጊዜ ያለው አስፈሪ ዝምታ ማለት አይደለም። የግንቦት7 መሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደገለፁት ለሰላም ብለን ባርነትን አንቀበልም። አባማም ያሉት ይህንኑ ነው።

**ርዕሰ አንቀጽ**

## ባራክ ኦባማ አምባገነኖችን ከስልጣን ለማውረድ ጦርነት አስፈላጊ መሆኑን ተናገሩ

አሜሪካዊው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ አምባገነኖችን ለማውረድና ሰላምን ለማስፈን አንዳንድ ጊዜ ሀይልን መጠቀም ብቻኛ አማራጭ መሆኑን ታሪክ አስተምሮናል ሲሉ ለነጻነት የሚደረጉ ጦርነቶችን ደግፈው ተናግረዋል። ፕሬዝዳንቱ ከቀናት በፊት የኖቬል የሰላም ሽልማታቸውን ሲቀበሉ እንደተናገሩት የሰላማዊ ትግል አራማጆች የነበሩት ማህተመ ጋንዲና ማርቲን ሉተር ኪንግ የሚደነቁ ሰዎች ናቸው፣ ይሁን እንጅ የእነሱ የሰላማዊ ትግል ስትራቴጂ ሂትለርን ጦር ከመምዘዝ አይገታውም። ውይይት አልቃይዳን ወደ ጠረጴዛ ድርድር አያመጣውም፣ መሳሪያውን እንዲያስቀምጥም አያደርገውም። ሀይል አንዳንድ ጊዜ ያስፈልጋል ብሎ መናገር ግብዝ አያስብልም፤ እንዲያውም ለታሪክ እውቅና መስጠት ነው ብለዋል። ፍትሀዊ ጦርነት ብለው ከዘረዘሩዋቸው የጦርነት አይነቶች መካከል ራስን ለመከላከል የሚደረግ ጦርነት፣ የተወረረችን አገር ለመርዳት የሚደረግ ጦርነትና ሲቪሎች በአምባገነኖች ሲገደሉና ሲሰቃዩ እነርሱን ለመከላከል የሚደረግ ጦርነት ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን፣ ጦርነት ሲደረግ ስርአት ባለው መልኩ መደረግ እንዳለበትም ገልጸዋል። ሰላም ማለት የጦርነት አለመኖር ሳይሆን የዜጎችን የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችን ማክበር፣ ዜጎች ሀሳብን በነጻነት እንዲገልጹ መፍቀድ፣ የስራ እድልና ሀብት የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት መሆናቸውን አጽንኦት ሰጥተው የተናገሩት ፕሬዝዳንት ኦባማ በአለም ላይ ጦርነት ይኖራል ለሰላም መስራታችንን ግን አናቆምም በማለት ለነጻነት የሚደረጉ ትግሎችን በአወንታዊነት እንደሚያዩ ገልጸዋል

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## መለስ ዜናዊ የአሜሪካ አምባሳደርን “ደደብ ” ሲል ዘለፈ። በጋራ መንግሥት ምስረታ ኢህአዴግን በሂደት መቀየር ይቻላል የሚሉትንም አስጠነቀቀ።

ኮፐን ሃገን በሚደረገው የአለም አየር ለውጥ ስብሰባ ላይ አፍሪካን ወክሎ ለመገኘት በቢጤዎቹ የአፍሪካ አምባገነኖች የተወከለው ዘረኛው መለሰ ዜናዊ፤ በተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች አመታዊ የግምገማ ጉባኤ ላይ ባለፈው ሳምንት በተለይ በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ ያሉት የስልጣን እርከኖች በሙሉ ከራሱ ብሄረሰብ በመጡ ሰዎች መሙላቱን የተቹትን አሜሪካዊ አምባሳደር ደደብ መሆን አለባቸው ሲል መሳደቡን ተሰምቶአል። ከአገር ውስጥና ውጪ እየተቀጣጠለ ባለው ተቃወሞ በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ የተዘፈቀው መለስ ዜናዊ፤ ከአንድ ሳምንት ባነሰ ጊዜ ውስጥ 3 ተከታታይ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ለመስጠት እንደተገደደ የተስተዋለ ሲሆን ከጋዜጠኞች ለቀረቡለት በርካታ ጥያቄዎች የሰጣቸው መልሶችም ድንፋታ ፤ ቁጣና የእብሪተኝነት ስሜት የተንጸባረቀበት እንደነበር ተስተውሎአል። ይህም ያለበትን ከፍተኛ የሆነ ስጋትና መረበሽ በግልጽ የሚያመለክት ነው የሚሉት የፖለቲካ ተንታኞች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አሉኝ ብሎ ይመካባቸው የነበሩት ድጋፎች መሰረታቸው ከውስጥና ከውጪ እየተናዱ መሆኑን በመገንዘቡ የደረሰበት የስነ-ልቦና ቀውስ እንደሆነ ይስማሙበታል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር በይፋ ባሰራጨው ማስረጃ ፤ በመከላኪያ ሠራዊቱ ውስጥ በአዛዥነት ካሉት 62 የጦር መኮንኖች 58ቱ በትግራይ ብሄረሰብ አባላት መያዛቸውን እስከነ ሥም ዝርዝራቸው ማሳወቁ የሚታወስ ሲሆን ይህንን በአደባባይ ገጦ የወጣን ሃቅ ለማስተባበል የተቸገረው መለስ ዜናዊ የገባበትን ቅሌትና የተዘፈቀበትን ሁዋላ ቀር ዘረኝነት ለመሸፈን መንግሥቱ ሃይለማሪያም ተስፋ በቆረጠበት የመጨረሻዎቹ ስልጣን ዘመኖቹ ያደርግ እንደነበረው በስድብና ዘለፋ የተሰማውን ንዴትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይገልጽ ከነበረበት ሁኔታ ጋራ የተመሳሰለ ክስተት አመልካች ነው ተብሎአል ።

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የነፍሰ ገዳዩና ዘረኛው መለስ ዜናዊ በኮፔን ሃገኑ ጉባኤ ላይ መገኘትን በመቃወም ታላቅ ሠላማዊ ስልፍ እየተካሀደ ነው፤ የአፍሪካን ጥቅም አሳልፎ በመሰጠቱም ተወነጀለ

ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በደንማርክ ዋና ከተማ በኮፔን ሃገን እየተካሄደ ባለው አለም አቀፍ የአየር ብክለት ጉባኤ ላይ ለድርድር አፍርካን ወክሎ የተላከው መለስ ዜናዊ፤ በሥልጣን ላይ በቆየባቸው 19 ዓመታት ውስጥ በፈጸማቸው ዘርፈ ብዙ ወንጀሎች ምክንይት አለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍ/ቤት መቅረብ ሲገባው በእንዲህ አየነቱ መድረክ መገኘት የለበትም የሚሉ ኢትዮጵያዊያን የተለያዩ መፈክሮችን ይዘው ጉባኤው ከሚካሄድበት አዳራሽ ፊት ለፊት ተቃውሞአቸውን በማሰማት ላይ እንደሚገኙ በዛሬው ታህሳስ 9 ቀን ይህ ጋዜጣችን ለህትመት ከመግባቱ ግማሽ ሰዓት በፊት የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።

እንደሪፖርተራችን ዘገባ ሰላማዊ ሠልፈኞቹ ተቃውሞአቸውን ለማሰማት ከተለያዩ የአውሮጳ አገሮች በየብስ፤ በባህርና በአየር ረዥም ርቀት ተጉዘው የመጡ መሆናቸው ሲታወቅ ለበርካታ ወገኖቻችን በጠራራ ጸሃይ በአጋዚ ጦር መጨፍጨፍ፤ መታሰርና ከአገር መሰደድ ምክንያት የሆነው ይህ ከዘመናችን ጨካኝ አምባገነኖች የመጨረሻው ደረጃ ላይ የሚገኝ ኋላ ቀር ሰው አፍሪካን ወክሎ እንዲገኝ መደረጉ እጅግ አበሳጭቶአቸው እንደሆነ ያነጋገራቸው ሰልፈኞች ገልጸዋል;፡

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ኢትዮጵያ ሳይታሰብ ሊፈነዳ በሚችል ቦምብ ላይ መሆንዋን አንድ የጥናት ውጤት በጀርመን አገር ገለጸ

በሀገሪቱ እያንዣበበ ባለው አስከፊ ርሃብ: እየተበራከተ የመጣው ስራ አጥነት: የኑሮ ወድነትና የሰብአዊ መብት ጥሰት በዚሁ ከቀጠለ ሃገሪቱ ሰዓት ጠብቆ በሚፈነዳ ቦምብ ላይ መሆንዋንና: ያልታሰበና አድገኛ ወደሆን ብጥብጥ ልታመራ እንደምትችል ለረጅም ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ ጥናት ያካሄዱ አንድ ምሁር አስታወቁ። በኖርዌይ ዩኒቨርሲቲ የሰብዓዊ መብቶችና ዓለም ዓቀፍ ህግ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ትሮንት ፎል ይህንን ያሳሰቡት በኢትዮጵያን እያንዣበበ ያለውን የፖለቲካ ድባብ ለመቃኘት ታዋቂ ምሁራን: የሰብአዊ መብት ተሚጋቾችና የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ባለፈው አርብ በጀርመን ርእሰ ከተማ በበርሊን ላይ ባደረጉት ሴሚናር ነው።

አንድ አገር በአንድ አገዛዝ ስር ለረዥም ዓመታት መቆየት ለከፋ ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀዉስ አገሪቱን እንደሚዳርግ ምሁሩ ጨምረው ገልጸዋል።

**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## ወያኔ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ለማስመረጥ በአዲስ አበባ ከተማ በጠራው ስብሰባ የራሱን አባላትና ደጋፊዎች ብቻ ማስመረጡ ታወቀ

የግንቦት 7 ዜና ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን የዜና ዘገባ መሰረት፣ወያኔ በቅርቡ ከአንዳንድ ተቃዋሚ ነን ከሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በተፈራረመው የስነ-ምግባር መመሪያ ድንብ መሠረት ለመጪው ምርጫ ተብዬ የወያኔ ድራማ በአስፈጻሚነት የሚያገለግሉትን ገለልተኛ ሰዎች ለማስመረጥ በሚል ሰበብ ባለፈው ዕሁድ ታህሳስ 4 ቀን 2002 በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ ቀበሌዎች በጠራው ስብስባ የራሱን ታማኞች ማስመረጡ ታውቆአል። በአብዛኛው ቀበሌዎች የነበረውን የምርጫ አካሄድ ተዘዋውሮ የተመለከተው ሪፖርተራችን እንደዘገበው፣ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የተካሄደው የምርጫ ሥነ-ሥረዓት ተመሳሳይነት ያለው እንደነበረና አስቀድሞ በተዘጋጀ ድርጅታዊ ሥራ ቀደም ሲል ወያኔ ለዚሁ ተግባር አሰልጥኖ ባዘጋጃቸው ካድሬዎች ስብሰባ መሪነትና ጠቋሚነት በወያኔ ደጋፊነታቸው የሚታወቁ ወይም በአባልነት የሚሰሩ ሰዎች እንደተመረጡ ለማወቅ ተችሎአል። በምርጫ 97 የተሰራውን ስህተት ላለመድገም እየማለ እየተገዘተ ያለው የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ቡድን በየቀበሌው እጩዎችን የሚጠቁሙ ሰዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብና ፣ መድረኩን የሚመሩት ደጋፊዎቹ የዕጩ ጥቆማ ሲካሄድ እድሉን ለማን መስጠት እንዳለባቸው አስቀድሞ በማዘጋጀት አይን ባወጣ ማጭበርበር ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ ያለፈው ስህተት እንዳይደገም በቂ ዝግጅት ተደርጎአል በማለት መለስና በረከት ጉራ ሲነዙ የነበሩት ምን ለማለት እንድሆነ ገና ከጅምሩ በተግባር አሳይቶዋል ተብሎአል ። መድረኩን የሚመሩት ሰዎች የመጠቆም የቤት ስራ ከተሰጣቸው የወያኔ ሰዎች ውጭ ሌሎችን ገለልተኛ ወገኖች እድል አለመስጠታቸውን ለማረጋገጥ የቻለው ሪፖርተራችን፣ ህዝቡም ሲደረግ በዋለው የፌዝ ምርጫ ሲያሾፍ መደመጡን ተናግሯል። ድሮውንም ነጻ ምርጫ እንደማይኖር እናውቃለን ያሉ አንድ አስተያየት ሰጪ፣ ወያኔ ነጻ ምርጫ የሚያደርገው በመቃብሩ ላይ ብቻ ነው ሲሉ ቁጭታቸውን ገልጸዋል።

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ነፃነታችንና ክብራችን የተጠበቀበት ሰላም ለማምጣት ወያኔን ማስወገድ የሞራልና የተፈጥሮዓዊ ግዴታችን መሆኑን አምነን ቆርጠን ተነስተናል!!!

ሰሞኑን ፕሬዚዳንት ባራክ አባማ የኖቬል የሰላም ሽልማት ሲቀበሉ ለበርካታ የሃገራችን ፓለቲከኞች ዓይን ከፋች ሊሆን የሚችል ቀልብ ሳቢ ንግግር አድርገዋል። ይህ ንግግር ከመነሻው እስከ መጨረሻው ያተኮረው ሰላማዊ የትግል አማራጭ ከወታደራዊ መፍትሄ እጅግ የተሻለ ስለመሆኑ የማያከራክር ቢሆንም በሰላማዊ መንገድ ብቻ ተጉዞ ሰላምን ማምጣት የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩ፤ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ኃይልን መጠቀም ግዴታ ብቻ ሳይሆን ከሞራል አንፃር ተገቢ ስለመሆኑ ያብራሩበት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎችና ሁኔታዎች የኃይል አማራጭ ተገቢነት እየጨመረ መምጣቱን እና ለሰላም ሲባል ደም አፍሳሽ ጦርነት ውስጥ እንኳን ሊገባ እንደሚችል ማስረጃዎችን በመጥቀስ ያስገነዘቡበት ነው።

ይህ የአባማ ንግግር ለአገራችን የወቅቱ ፓለቲካ ትልቅ ትርጉም ስላለው አለፍ አለፍ እያልን ከንግግራቸው እንጥቀስ፡-

> *እውነቱን በመቀበል እንጀምር – ብጥብጥ ያለበት ቅራኔን በእኛ እድሜ ማስቀረት አንችልም። ለወደፊቱም ሕዝቦች – በግልም ሆነ በጋራ – ኃይልን መጠቀም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ከሞራል አንፃርም ተገቢ የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል።*

ይህን አባባል ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እንተርጉመው። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሁለገብ ትግልን እንደ አማራጭ ሲያቀርብ የሰላማዊ ትግልን ውበት በመጠራጠር አልነበረም። በደምሳሳው ከታየ የኃይል አማራጭ የሚያስከፍለው የሕይወት ዋጋ ከፍተኛና አሰቃቂ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ብዙውን ጊዜ ደግሞ በኃይል የተያዘን ሥልጣን በሰላም ለመልቀቅ ያስቸግራል ተብሎም ይታመናል። ይሁን እንጂ ሁለቱ እምነቶች እውነት የማይሆኑበት እድል ከፍተኛ ነው። እንደወያኔ ዓይነት ይሉኝታ ቢሶች ሥልጣን በያዙበት አገር "ሰላማዊ" ሰልፍ ከጦርነት የባሰ የበርካታ ንፁሃን ሕይወት መጥፊያ ሊሆን ይችላል። በሰላማዊ ምርጫ ሥልጣን ይዘው የሙጥኝ ያሉ አጭበርባሪዎች እንዳሉ ሁሉ በኃይል ሥልጣን ከያዙ በኋላ ለሕዝብ ምርጫ የተገዙ ልባሞችም አሉ። ስለሆነም በዚህ ጉዳይም ላይ አንድ ዓይነት የማያሻማ ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም። ክርክር የማያሻው ሃቅ በሰላማዊ ትግልና ባነሰ ዋጋ ነፃነትን ማግኘት እየተቻለ በኃይል ለመንጠቅ የመሞከር ጀብደኝነት ተቀባይነት የማይኖረው መሆኑ ነው። ሰላማዊ ትግል ነፃነትን ማስገኘት የማይችል ከሆነ ግን በሰላማዊ ትግል ስም ባርነትን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን "የሰለጠነ ፓለቲካ" ሳይሆን "ዘመናዊ ባርነት" ብቻ ነው የሚሆነው። አባማም ቀጥሎ ባለው አንቀጽ ያስገነዘቡን ይህንኑ ነው።

> *አንሳሳት! ክፉት በዓለም ላይ አለ። በሰላማዊ ትግል ሂትለርን መግታት አይቻልም ነበር። ድርድር የአልቃይዳን መሪዎች መሣሪያዎቻቸውን እንዲጥሉ አያደርግም። አንዳንዴ ጉልበት መጠቀም ያስፈልጋል ማለት ከሃቅ የራቀ ምፀት አይደለም፤ ይልቁንስ ታሪክን በቅጡ መረዳት፤ የሰውን ልጅ ድክመቶችን ማወቅ እና የምክንያታዊነት ውስንነትን መገንዘብ ነው።*

ግንቦት7 ምርጫ 97ን ገምግሞ የትግል ስልቱን በቀየሰበት ሰነዱ (ሀ) ሰላማዊና ህጋዊ የሆነ የትግል ስልት፣ (ለ) ሰላማዊ ሆኖ ህጋዊ ያልሆነ የትግል ስልት እና (ሐ) ሰላማዊም ሕጋዊም ያልሆነ የትግል ስልት ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን መርምሮ መለስ ዜናዊ ህግ ብሎ ለሚጠራው ባርነት የማይገዛ ለሰላማዊ ትግልም ለአመፃም እድል የሚሰጥ ከላይ በተዘረዘሩት የትግል ስልቶች ውስጥ ያሉትን ጠንካራ ጎኖችን ወስዶ **ሁለገብ የትግል ስልትን** መርጧል። ይህ ስልት ለመለስ ህግ የማይገዛ የሰላማዊና የአመፃ አማራጮችን በሙሉ እንደሁኔታው የሚጠቀም ነው።

በወቅቱ የአመፃን አማራጭ ክፍት በማድረጋችን አንዳንድ ወገኖቻቸን ይህ ስልት ከበርሊን ግንብ መፍረስ ጋር ጊዜው ያለፈበት አማራጭ ነው ሲሉ ነበር፤ አሁንም በተመሳሳይ የሚያስቡ አይጠፉም። በአስሎው የኖቬል ሽልማት አዳራሽ ውስጥ የፕሬዚዳንት አባማ ንግግር ለዚህ አጥጋቢ ማብራሪያ የሰጠ ይመስለናል።

> *ሲቪል ዜጎች በገዛ መንግሥታቸው የሚታረዱበት ሁኔታ፤ የእርስ በርስ ጦርነቶች ወይም አንድን የዓለም አካባቢ ሊያምሱ የሚችሉ ብጥብጦችና ሰቆቃዎችን ለመከላከል ኃይልን የመጠቀም አማራጭ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል።*

ሰላምን መመኘት፣ ስለሰላም መዘመር፣ ስለሰላም ማስተማር፣ ስለሰላም መስበክ በእርግጥ ሰላምን ያስገኛል? ሰላም የሚደፈርሰው ሰዎች ስለሰላም ጥሩነት በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው ነውን? በጭራሽ! ሰላምን መመኘት፣ ስለሰላም መዘመር፣ ማስተማርና መስበክ ጥቅም ቢኖራቸውም ሰላምን ለማስገኘት በቂ አይደሉም፤ ሆነውም አያውቁም።

> *ሰላም ተመራጭ መሆኑ መታመኑ ብቻውን ሰላምን ለማስገኘት አይበቃም። ሰላም ኃላፊነት መቀበል ይጠይቃል። ሰላም መስዋዕትነትን ይጠይቃል።*

በሰላም ስም ባርነትን ማስፈን የአምባነገነኖች አንድ የጋራ ባህርይ ነው። አምባገነኖች ሰላም ማለት ሁሉም ሰው ከገዢዎች ተቆንጥሮ የሚሰጠውን መብት አመስግኖ ተቀብሎ፤ እንዲጫወት የታዘዘውን ባህርይ እየተጫወተ መኖር ማለት አድርገን እንድንወስድ ይፈልጋሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሰላም፣ ነፃነትና ክብር የማይነጣጠሉ ነገሮች መሆናቸውን ነው። ስለ ሰላም ማሰብ የምንፈልገው ሙሉ ስብዕናችን በተረጋገጠበት ሁኔታ እንጂ ስብዕናችን በተዋረደበት ጊዜ ያለው አስፈሪ ዝምታ ማለት አይደለም። የግንቦት7 መሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደገለፁት ለሰላም ብለን ባርነትን አንቀበልም። አባማም ያሉት ይህንኑ ነው።

> *ሰላም የሚታይ ብጥብጥ አለመኖር ማለት አይደለም። ፍትሃዊ ሰላም ዘላቂነት የሚኖረው በእያንዳንዱ ግለሰብ ተፈጥሮዓዊ መብቶችና ክብር ላይ የተገነባ ሲሆን ነው።*
>
> *.......*
>
> *ዜጎች የመናገር፣ የማምለክ፣ መሪዎቻቸውን የመምረጥ ወይም ያለፍርሃት የመሰብሰብ ነፃነታቸው በተገፈፉ ጊዜ ዘላቂ ሰላም አይኖርም። .... እንደምናውቀው አውሮፓም ሰላም ያገኘችው ነፃ ስትሆን ነው።*

ኢትዮጵያዊያን የገጠመን ፈተና ፕሬዚዳንት አባማ ከገለፁት የመናገር፣ መሪዎቻችንን የመምረጥና የመሰብሰብ መብት ማጣት ብቻ አይደለም። የተፋጠጥነው የዛሬ መብቶቻችንን ብቻ ሳይሆን የነገ ተስፋችንንም ሊያጨልምብን ከሚሞክር መሰሪ ሥርዓት ጋር ነው። በወያኔ አገዛዝ ዜጎች ተዋርደውና ተሸማቀው አሜን ብለው እንዲገዙ መደረጉ ብቻ ሳይሆን እንደ ሕዝብና እንደ አገር የመቀጠላችን ጉዳይ አጠራጣሪ እየሆነ በመምጣቱ ነፃነታችንና ክብራችን የተጠበቀበት ሰላም ለማምጣት ወያኔን ማስወገድ ግዴታችን መሆኑን አምነን ቆርጠን ተነስተናል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

## ኢትዮጵያ ሳይታሰብ ሊፈነዳ በሚችል ቦምብ ላይ

.. ከገጽ 1 የዞር

ፕሮፌሰር ትሮንት ፎል ባለፉት 20ዓመታት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ይዞት ላይ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን ኢትዮጵያ ያስጋታል ያሉትን የፖለቲካ እንደምታዎች በአራት ክፍሎች በመክፈል አቅርበዋል። የመለስ ከስልጣን በገዛ ፈቃዱ መውረድና ይህ በራሱ ፓርቲና ውጪ ሊያስከትል የሚችለው የፖለቲካ ለውጥን ምሁሩ በመጀመሪያ ደረጃ የቃኙ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሚሊዮኖች የሚቆጠር በኑሮ የተከፋ የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይታሰብ በስርዓቱ ላይ ሊነሳ እንደሚችል ገልጸዋል:: በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በአንድ ጊዜ ቢነሳ የመለስ ዜናዊ ሰራዊት ገድሎ ሊጨርስ እንደማይችልና ከቁጥጥሩ ውጪ ሊሆንበት እንደሚችልም ፕሮፌሰር ትሮንት ፎል አስገንዝበዋል። ከዚህም ውጭ አንድ ያልታሰበ ነገር ፈንድቶ ሁኔታዎች ባልተጠበቀ ፍጥነት ይቀየርና የአምባገነንነት ፍጻሜ ሊሆን ይችላል ካሉ ቦኋላ በአራተኛነትም የመለስ አደገኛ የፖለቲካ አቅጣጫ በአገሪቱ ውስጥ ሊያመጣው የሚችለው የእርስ በርስ ጦርነት ለምስራቅ አፍርካና ከዚያም ውጭ ላሉት አገሮች ሰለ ሚተርፍ አደጋ ያደረባቸውን ስጋት ገልጸዋል። በስብሰባው ላይ ለመገኘት ከአገር ውስጥ የተጋበዙ ፖለቲከኞች የፕሮፈሰሩን በጥናት የተደገፈ ትንቢያ ሳያስተባብሉ የተጠቆሙት ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ህዝባችን ተግቶ መታገል እንዳለበት ወያኔ ኢህአደግም ለህዝብ ፈቃድ ለመገዛት ጊዜው እንዳላልፈበት አስምረውበታል ። ፕሮፌሰር ትሮንት ፎል በምርጫ 97 ወቅት እና ከምርጫ 97 በፊት በኢትዮጵያ ተደረገው በነበሩት ምርጫዎች ቋሚ ታዛቢም ነበሩ።

# ሃይለ ሀሳብ

## ረሀብን ለማጥፋት መሬትን ለባዕዳን መሸጥ የሚለውን አዲሱ የመለስ ዜናዊን የኤኮኖሚ ፖሊሲ መታገል የሁላችንም ሃላፊነት ነው !

ኤፍሬም ማዴቦ

ወታደራዊዉ የደርግ መንግስት ካወጣቸዉ አዋጆች ሁሉ የገጠርን መሬት ለህዝብ ያደረገዉ አዋጅ በአይነቱ ልዩ የሆነ ስር ነቀል አዋጅ ነበር። ይህ አዋጅ በባላባትና በገባር መካከል የነበረዉን በብዝበዛ ላይ የተመሰረተ የምርት ግኑኝነት በመበጣጠስ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ያመረቱት ምርት ብቸኛ ባለቤቶች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡ ሆኖም ደርግ ሶሻሊዝምን ከመከተሉ ባሻገር ገበሬዉ መሬቱን መሸጥ፤ መለወጥ ወይም በወለድ አግድ ማስያዝ እንዳይችል በማድረጉና በአጠቃላይ የገበሬዉን የመሬት ባለቤትነት በመቀማቱ ደርግ ያወጀዉ ስር ነቀል የመሬት አዋጅ በአገራችን የምግብ ምርት አቅርቦት ላይ ለዉጥ ማምጣት አልቻለም። ከመሬት አወጁ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የደርግ አገዛዝ የምርት ዘመቻ የሚል እንቅስቃሴ ጀምሮ ብዙ የእርሻ መሳሪያዎችን አስመጥቶ የምግብ ምርትን ለማሳደግ ቢሞክርም የተከተለዉ የሶሻልስት ስርዐት ለምርት እድገት አመቺ ባለመሆኑ ከ1976 እስከ1977 በነበሩት ሁለት ዐመታት አገሪቱን ቀስፎ የያዘዉ ረሀብ በመቶ ሺዎች የሚቀቆጠሩ ወገኖቻችንን ህይወት ቀጥፏል።

ወታደራዊዉን ደርግ አሸንፎ አዲስ አበባን የተቆጣጠረዉ ወያኔ ኢትዮጵያን የነፃ ገበያ አገር አደርጋታለሁ ብሎ ምሎ ቢገዘትም በተግባር እንደምናየዉ ግን የኢትዮጵያን ገበሬ ከደርግ በወረሰዉ የኮሚኒስት የመሬት ፖሊሲ እጅና እግሩን አስሮ አገራችን ኢትዮጵያን ዛሬም እንደገና አለም አቀፍ የምግብ ለማኝ አድርጓታል።ሌሎች ከፈጸሙት ልማትም ሆነ ጥፋት ትምህርት የመቅሰም ባህሪይ አብሯቸዉ ያልተፈጠረዉ የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያን ሶቭዬት ህብረት፤ ቻይናና ምስራቅ አዉሮፓ ዉስጥ ተሞክሮ ዉድቅ የሆነ ኅታች የመሬት ይዞታ ፖሊሲ መሞከሪያ ቦታ አድርገዋታል። ዛሬ የአለማችን የስልጣኔ ቁንጮ የሆኑ አገሮች አሁን ያሉበት የእድገት ደረጃ ላይ የደረሱት ከኛ ወደ ኃላ ከቀረነዉ አብልጠዉ ወይም ጠንክረዉ ስለሰሩ ብቻ አይደለም። በታታሪነትና ጠንክሮ በመስራት ብቻ እድገት የሚገኝ ቢሆን ኖሮ ዱንጋይና ጉቶ ከሁለት በሬዎቹ ጋር እየፈነቃቀለ ከሚያርሰዉ የኢትዮጵያ ገበሬ በላይ ጠንክሮ የሚሠራ ታታሪ ሰራተኛ የለም። ኃብታም አገሮችን ኃብታም ያደረገዉ ያዋቀሩት የምርት ግኑኝነትና የሚከተሉት የኤኮኖሚ ፖሊሲ እድገትን የሚያፋጥን ብቻ ሳይሆን የእድገትን መንፈስ የሚያበረታታና የሚሸልም በመሆኑ ነዉ።

ዛሬ ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚከተለዉ የኤኮኖሚ ፖለሲ የራሴ የሚላቸዉን ጥቂቶች የሚያደልብ ሌሎችን ወይም ብዙኃኑን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያቀጭጭ በአድሎና በዘረኝነት ላይ የተመሰረተ የኤኮኖሚ ፖለሲ ነዉ። ለዚህ ነዉ ዛሬ ባዶ እጃቸዉን አዲስ አበባ የገቡት እነ ስብሐት ነጋ፤አዜብ መስፍን፤ በረከት ስምኦንና አባዲ ዘሙን የመሳሰሉ ዘራፊዎች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ለንደንና ዙሪክ ባንኮች ዉስጥ መቆለል የቻሉት።

አገራችን ኢትዮጵያ መሬት የባላባቶች በነበረበት የፊዉዳል ስርዐት ዉስጥ አልፋለች፤ የዚህ አስቀያሚ ሰርዐት ምልክትና የዉድቀቱ ዋነኛ መንስኤ የብዙዎችን ህይወት የቀጠፈዉ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተከሰተዉ ድርቅ እንደነበር የሚታወስ ነዉ። ወታደራዊዉ ደርግ የፊዉዳሉን የምርት ግንኙነት አፍርሶ መሬትን የህዝብ ንብረት ቢያደርግም እሱ ራሱ በደምብ የማያዉቀዉን ሶሻሊዝምን ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማስተዋወቅ በመሞከሩ ኢትዮጵያ ዉስጥ የምግብ ምርት አቅርቦትን ለማሳደግ የነበረዉን እድል ሳይጠቀምበት ቀርቷል።

ዛሬ የምኒልክን ቤተመንግሰት በኃይል የተቆጣጠሩት የወያኔ ዘረኞች ከጫካ ወጥተዉ አዲስ አበባ ሲገቡ ለህዝብ የገቡት ቃል - ኢትዮጵያ ረሀብን፤ጦርነትንና አምባገነን መሪዎችን እንደገና አታይም የሚል ነበር። ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት 18 ዐመታት ሁለት የማያስፈልጉ ጦርነቶችን፤ሁለት የረሀብ ወቅቶችንና መለስ ዘናዊን የመሰለ በዘር ማጥፋት ወንጀል የሚፈለግ አምባገነን ገዢ አይቷል።

የህዝብ መብትና ነፃነት መረገጥ፤ኅታች የመሬት ይዞታና ተደጋጋሚ የረሀብ አደጋ መከሰት ለፊዉዳሉና ለወታደራዊ ደርግ ስርአቶች መዉደቅ አይነተኛ ምክንያቶች ነበሩ። የሚገርመዉ የዛሬዎቹ ወያኔዎች የኢትዮጵያ ህዝብ በደርግ አገዛዝ ላይ በምሬት እንዲነሳ ማድረግ የቻሉት እነዚሁኑ ሦስት መሰረታዊ ችግሮች ህዝብ በሚገባ እንዲያዉቃቸዉ በማድረግ ነበር። ዛሬ የመለስ ዜናዊ ስርአት የተለያየ ሽፋን እየፈለገ የሰራቸውን ወንጀሎች ለመሸፈን ቢሞክርም እንደ ተራራ የተቆለለ ሆኖአልና የሚሳካለት አልሆነም። ሺህ ጊዜ መልሶ መላልሶ ገና ዕዳው ለልጅ ልጅ በሚተርፍ ከፈረንጆች በተገኘ ብድር የተዘረጋውን የአስፋልት መንገድ ሰርቸልሃለሁ ብሎ ዋቢ ቢጠቅስ ፤ በየከተማው ትላልቅ ህንጻዎች ጉች ጉች አድርጌልሃለሁ ብሎ ቢቀባጥር ማን ሊሰማው ? ደግሞስ ትናንት ለእግራቸው እንኳ መጫሚያ ያልነበራቸው ተጋዳላዮች ከህዝብ በተዘረፈ ሃብት በአንድ ምሽት መክበር አንሶአቸው ለዘመናት በጭሰኝነት ሊገዙን ሲፈልጉ ይህ ውርደት መሆኑን ማን ይሰተዋል? እዚህ ላይ ለነፃነቱ የሚታገለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አጥብቆ እንዲገነዘበዉ የምንፈልገዉ አንድ ትልቅ ቁምነገር አለ። በአብዛኛው የአለማችን ክፍሎች የፖለቲካ ሥልጣን ህዝብ ለወደደዉና ላመነዉ አካል የሚሰጠዉ ህዝባዊና አገራዊ አደራ ነዉ እንጂ ማንም በኃይል እየያዘዉ ህዝብን የሚረግጥበት መሳሪያ መሆኑ ከቀረ ዉሎ መሰንበቱን ነው ። ስለዚህ ኢትዮጵያ ዉስጥ የህዝብን መብትና ነፃነት የሚያከብር በህዝብ የተመረጠ መንግስት ስልጣን አስካልያዘ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ ለአንድም ቀን ቢሆን ትግሉን ማቆም የለበትም።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች ዉስጥ የኤኮኖሚ እድገትን ለማፋጠንና የኑሮ ደረጃን ለማሳደግ በሚደረገዉ ትግል የግብርናዉ ዘርፍ የሚጫወተዉ ሚና እጅግ በጣም ትልቅ ነዉ። ኋላ ቀር የሆነዉንና አብዛኛዉን የአገራችንን ህዝብ ያቀፈዉን የግብርና ዘርፍ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሳናደራጅና ይህ ዘርፍ ሊያመነጭ የሚችለዉን የካፒታል ክምችት በሚገባ ሳንጠቀም የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ አደገ ማለት በፍፁም አንችልም። የግብርናዉ ዘርፍ እንዱስትሪን ለመገንባት የሚያስችለንን ከፒታል ማመንጨት ብቻ ሳይሆን እያደገ ለሚሄደዉ የእንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች ጥሬ ዕቃና የሰዉ ኃይል ማቅረብ የሚችል የዕድገት መሠረት የሆነ ዘርፍ ነዉ።

ዛሬ መሬትን በተመለከተ መለስ ዜናዊ አገራችን ኢትዮጵያን መዘዙ የማያልቅ አጣብቂኝ ዉስጥ እየከተታት ነዉ። ለሁላችንም ግልፅ እንደሆነዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሚከተለዉ የመሬት ፖሊሲ የዕድገት ጠንቅ የሆነዉ የኮሚኒስቶች የመሬት ፖለሲ ነዉ። ይህ ፖለሲ በሌሎች አገሮች ብቻ ሳይሆን እኛም አገር ዉስጥ ተሞክሮ ህዝብ አንቅሮ የተፋዉ የዕድገት እንቅፋት የሆነ ፖሊሲ ነዉ።የኢትዮጵያን የመሬት ይዞታ አስመልክቶ ወያኔ ራሱ የፃፈዉ ህገ መንግስት መሬት የህዝብ ንብረት ነዉ ይላል፤ ሆኖም ወያኔ ህዝብ የሚለዉ ማንን እንደሆነ በዉል የሚታወቅ ነገር የለም- ምክንያቱም ወያኔ ለኢትዮጵያ ገበሬ የሚሰጠዉ አማካይ የመሬት መጠን ከ0.3 ሄክታር ያነሰ ሲሆን ለዉጭ አገር መንግስታትና ድርጅቶች ግን ከ3.5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በርካሽ ለመሸጥ ዝግጅቱን አገባዷል። ቀጣፊዎቹ የወያኔ ሹማምንት የመሬት ሽያጩን አስመልክቶ በተለያዩ መድረኮች የሚሰጡት ማብራሪያ እንኳን እኛን ኢትዮጵያዉያንን ብዙ የዉጭ አገር ታዛቢዎችን ያስገረመና ያሳዘነ ጉዳይ ነዉ። የመሬት ሽያጩን አስመልክቶ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ እንዲህ ነበር ያለዉ - "ይህ ፖሊሲ የምግብ እጥረት ችግራችንን ይፈታል ብለን እናምናለን እንዲህም ገበሬዉን ከአዲስ ቴክኖሎጂ ጋር በማስተዋወቅ ልማትን ያፋጥናል" መለስ ዜናዊ በዉሹቱና በጥላቻዉ እኛ ልንወዳደረዉ ከምንችለዉ በላይ ይበልጠናል ብለን እናምናለን። ለኢትዮጵያ ምን ይበጃታል የሚለዉን ጥያቄ በተመለከተ ግን ከኢትዮጵያ ህዝብ በተሻለ መልኩ መመለስ የሚችል አካል አለ ብለን አናምንም። እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ዜጋ ዉስብስብ የሆኑ የኤኮኖሚ ፖሊሲዎችንና የእድገት ስትራቴጂዎችን በቀላሉ አይረዳ ይሆናል፤ ሆኖም የቻይናና የሳዑዲ መንግስታት ኢትዮጵያ ዉስጥ አምርተዉ የራሳቸዉን ህዝብ ስለቀለቡ ኢትዮጵያ ዉስጥ የምግብ እጥረት እንደማይቃለል በሚገባ ይረዳል።

የአገራችን የኢትዮጵያን ዕድገት ለማፋጠን ብቸኛዉ አማራጭ የግብርናዉን ዘርፍ መለወጥ መሆኑ በተዳጋሚ ተገልጿል- እንደዚህ ሲባል ደግሞ የኢትዮጵያ ገበሬ ከሱና ከቤተሰቡ ፍጆታ በላይ ከፍተኛ ተረፈ ምርት እንዲያመርት ማስቻል አለብን ማለት ነዉ፤ ሆኖም እንደዚህ አይነቱ የዕድገት ግብ ከ .3 ሄክታር ያነሰ መሬት ባለዉና በመቀናጀ በሚያርስ ገበሬ አቅም የሚታለም አይደለም። ስለዚህ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሚሰማ ከሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ መሬት ለባዕዳን በርካሽ ከመቸርቸር ይልቅ የሚታረስ መሬት አጥቶ ለሚሰቃይ ገበሬ መሬት ቢሰጥ ይሻለዋል- አለዚያ ባላባቶችንና ወታደራዊ አምባገነኖችን የቀጣዉ የአትዮጵያ ህዝብ ክንድ በዘረኞች ላይ የሚነሳበት ግዜ በቀኖች የተቆጠረ ነዉ፡

የአገራችን ዳር ድንበር በወራሪዎችና በተስፋፊዎች በተደፈረ ቁጥር የቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ነገስታት ህዝብ አገሩን እንዲከላከል ጥሪ የሚያደርጉለት መሬትህን የሚወሰወድ ጠላት መጣብህ እያሉ ነበር። ለነፃነቱና ለዳር ድንበሩ ቀናኢ የሆነዉ የኢትዮጵያ ህዝብም በየዘመኑ የነገስታቱን ጥሪ እየተቀበለ የእናት አገሩን ዳር ድንበር አስከብሯል። በአባቶቻችን ደም ዉስጥ የነበረዉ የአትንኩኝ ባይነት መንፈስ ደግሞ ዘሬም በኛ በልጆቻቸዉ ዉስጥ እንዳለ ነዉ፤ችግሩ በአባቶቻችን ግዜ መሬት ሊቀማ የሚመጣዉ ጠላት ባህር ተሻግሮ ነበር፤ ዛሬ ግን መሪ ተብዬዎቹ እራሳቸዉ ናቸዉ የአገራችንን መሬት ለባዕዳን ካልሰጠን እያሉ ከህዝብ ጋር ጦርነት ለመግጠም በዝግጅት ላይ የሚገኙት። በአፄ ዮሐንስና በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያ ጠላቶች ባህር ተሻግረዉ የሚመጡ ቅኝ ገዢዎችና ተስፋፊዎች ነበሩ፤ የዛሬዉ የኢትዮጵያ ጠላት ግን የኢትዮጵያ መሪ ነኝ የሚለዉ መለስ ዜናዊ እራሱ ነዉ። የረጂሙን ዘመን ታሪካችንን ትተን ያለፉት 150 ዐመታት ታሪካችንን ስንመለከት ኢትዮጵያ አያሌ ጨቋኝና አምባገነን መሪዎች ተፈራርቀዉባታል፡ ሆኖም በታሪካችን ዉስጥ ኢትዮጵያን የመራ ሰዉ በኢትዮጵያ መሬትና የግዛት አንድነት ላይ ተደራድሮ አያዉቅም። ዛሬ የኢትዮጵያን በትረ ስልጣን በኃይል የጨበጡት አምባገነኖች ግን ገና አዲስ አበባን ሲረግጡ ካሰሙን ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ንግግር አንዱ "ኢትዮጵያ ከተስማማን የምትኖር አለዚያም የምትጠፋ አገር ናት" የሚል መርዶ ነበር። እንግዲህ ለነዚህ ዘረኞች ለብዙ ሺ ዘመናት በአንድነቷ ፀንታ የዘለቀችዉ ኢትዮጵያ ልክ እንደ ቀበሌ ዕድር አባላቶች ሲስማሙ የምትዘልቅ ካልተስማሙ ደግሞ ምንግዜም ልትፈርስ የምትችል ግዜያዊ ክስተት ናት ማለት ነዉ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብና ኢትዮጵያ የሚገኙበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ አይቶትም ሰምቶትም የማያዉቀዉ እጅግ አደገኛ የሆነ ሁኔታ ነዉ፤ የዛሬዉ የኢትዮጵያ ጠላት እንደቀድሞዎቹ ጠላቶች የባዕድ ጦር አሰልፎ የመጣ ወራሪ ጠላት ሳይሆን የራሳችንን ልጆች አሰልፎ አለሁላችሁ እያለ ከጀርባ እየወጋ የሚጥል አደገኛ ጠላት ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ወያኔ የቀማህ መብትህንና፤ነፃነትህን ብቻ አይደለም። ወያኔ የቀማህ በህይወት ዘመንህ አርሰህ ልጆችህን የምትቀልብበትን ስትሞት ደግሞ በክብር የምትቀበርበትን መሬትህን ጭምር ነዉ። እጅግ በጣም የሚያሳዝነንና የሚነደን ነገር ቢኖር ይህ ዘረኛ አገዛዝ ላንተ ለመሬቱ ባለቤት የሰሰተዉን መሬት ነዉ ቁርስ የማያበላ ገንዘብ እየከፈሉህ ለሚበዘብዙህ የዉጭ አገር መንግስታት በሽያጭ የሚያድለዉ። አንድ ህዝብ ጠላትን የሚዋጋዉ ከዉጭ ስለመጣ ብቻ አይደለም፤ አንድ የተደራጀ ኃይል የህዝብን ነጻነት እስከቀማና ሰብዓዊ መብት እስከረገጠ ድረስ ነጭ ይሁን ጥቁር ከዉጭ ይምጣ ከዉስጥ ጠላትነቱን አይለዉጠዉም። ከላይ በግልፅ እንደተቀመጠዉ ወያኔ ደግሞ በዲሞክራሲ ስም ነፃነታችንን ለመርገጥ፤መሬታችንን ለመቀማትና ኢትዮጵያዊነታችንን ለማዳብዘዝ ቆርጦ የተነሳ ልዝብ ሰይጣን የሆነ ጠላት ነዉ። ይህ ጠላት ደግሞ ነገ ተደራጅተን እንዋጋዋለን እያልን ግዜ የምንሰጠዉ ጠላት አይደለም። ወያኔ እስትንፋስ ያለዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በየተሰማራበት መስክ በየቀኑ ሊታገለዉና በአጭር ግዜ ሊያስወግደዉ የሚገባ ጠላት ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ በአለማችን ዉስጥ ህዝብ ነፃነቱን ሳይታገል ያገኘበት ወይም የለየላቸዉ የህዝብ ጠላቶች በምርጫ ሥልጣናቸዉን ለህዝብ ያስረከቡበት የታሪክ አጋጣሚ የለም። የወያኔ ዘረኞች ደግሞ 17 አመት ታግለን አገኘን የሚሉትን ሥልጣን በምርጫ ሳጥን ለማንም አናስረክብም ብለዉ እቅጩን ነግረዉናል። ይህ መልኩን እየቀያየረና 5 አመት እየቆየ የሚመጣዉ ምርጫ የሚሉት ጨዋታ ለወያኔ አገዛዝ ህጋዊ ሽፋን ከመስጠትና የኛን የባርነት ዘመን ከማራዘም ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

የዚህ አመት የሰላም የኖቤል ሽልማት አሸናፊ የሆኑት ፕሬዚዳንት ባራክ አባማ ባሳላፍነዉ ሳምንት አስሎ ኖርዌ ዉስጥ ሽልማታቸዉን ሲቀበሉ ባደረጉት ንግግር የሰላማዊ ትግል አዉራ የሆኑትንና እንደሳቸዉ የኖቤል ሽልማት ተሸላሚ የሆኑትን ጋንዲንና ዶ/ር ኪንግን ካሞጋገሱ በኋላ እንዲህ ነበር ያሉት- "ሠላማዊ ትግል የሂትለርን ወራሪ ጦር ማቆም አይችልም ነበር፤ ድርድርና ዉይይት የአልቄዳን መሪዎች ወደ ሠላማዊ ኑሮ አያመጣም" አዎ! ባራክ አባማ አልተሳሳቱም እዉነታቸዉን ነዉ - በምርጫ፤በድርድርና በዉይይት የምንታገለዉ ባለጋራ አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሰላም ቋንቋ በፍፁም የማይገባዉና በምንም መልኩ ፊት ለፊት የሚታገለዉን ሁሉ ለመግደል የቆረጠ እንደወያኔ አይነቱ ጠላት አለ- ይህንን ጠላት አሸንፈን ነፃነታችንን ለማስከበር ያለን አማራጭ አንድ ነዉ- እሱም ለድል ያበቃናል ብለን የምናምነዉን ማንኛዉንም የትግል ስልት መጠቀም ነዉ -ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ - መብቴንና ነፃነቴን ረግጣችኃል አኔንና ልጆቼን ለረሀብ አጋልጣችኋል ብለህ ባስወገድካቸዉ ሁለት ስርአቶች ቦታ የተተካዉ ወያኔ ሰብዓዊ መብትህንና ነፃነትህን ከመርገጡ ባሻገር በዘረኝነት አለንጋ እየገረፈህ ነዉ። የዛሬዎቹ ጠላቶችህ አንተን ረግጦ ከመግዛት ባሻገር አገርህንም ከመገነጣጠል የማይመለሱ ናቸዉና ትናንት በአንድ ላይ ተነስተህ አልገዛም እንዳልክ ሁሉ ዛሬም ወያኔና መለስ ዜናዊ እኩይ እቅዳቸዉን ተግባራዊ ከማድረጋቸዉ በፊት ክንድህን አንሳና አገርህን ከአደጋ አድን።

## ባራክ ኦባማ አምባገነኖችን ከስልጣን ለማውረድ .. ከገጽ 1 የዞር

የኦባማ ንግግር ለነጻነታቸው በመታገል ላይ ለሚገኙ ንቅናቄዎች ሁሉ ትልቅ የሞራል ጥንካሬ እንደሰጠ ለንቅናቄያችን የተላኩት በርካታ መልእክቶች አመልክተዋል። አህዱ የተባሉ ጸሀፊ እንደተናገሩት ግንቦት 7 የሰላም ሀዋሪያ የሰላማዊ ትግል አርበኛ ንቅናቄ ነው። ግንቦት 7 ለሰላም ና ለሳማዊ ትግል ያለውን ፍቅር የሚክድ የለም ነገር ግን ሀይል ሰላምን ለማምጣት ሊያስፈልግ ይችላል ብሎ የሚያምንም ንቅናቄ ነው። የኦባማ ንግግር ያረጋገጠው ነገር ቢኖር የግንቦት 7 እምነት እና መንገድ ትክክል መሆኑን ነው ብሏል።

ስለሺ ማዘንጊያ የተባለ ጸሀፊ ደግሞ "ኦባማ የአምባገነኖችን ባህሪ ጠንቅቆ አውቆታል። በጭፍኑ ሰላማዊ ትግል ወይም ትጥቅ ብቻ አስፈላጊ ነው አላለም። እንደሁኔታዎች እያዩ መታገል ብልህነት መሆኑን አስምሮበት ተናግሯል። መለስ ዜናዊን የመሰለን አምባገነን በተገኘው መንገድ ከመታገል ሌላ ምን ፍትሀዊ ትግል ይኖራል? መለስና ሂትለር በምን ይለያያሉ። ያኛው የሰው አገር ሰዎችን በመግደሉ የሄኛው ደግሞ የራሱን ሰዎች በመግደሉ አይደለምን? እኛ ሂትለርን ለማውረድ ሀይል ካስፈለገ መለስን ለማውረድ ሀይል የማያስፈልግበት ምን ምክንያት ይኖራል?" ሲል ጠጥይቋል።

አቶ ክፍሌ ምህረት በበኩላቸው ኦባማ ከጋንዲና ከሉተር ኪንግ የተሻለ ያደነቀው የማንዴላን የትግል ስልት ነው። ማንዴላ የጋንዲን ትግል በመሞከር ሳይወሰን የሀይል ትግል ጨምሮ ታግሏል። ሀይል ፍትሀዊ የሚሆነው ሰላማዊ ትግልን ሞክረው ካዩት በሁዋላ ነው። ወደ ሀይል ከማምራት በፊት ሰላማዊ ትግልን ሞክሮ ማየት ያስፈልጋል። ኦባማም ይህን ምክር ነው የለገሰው። "ሲሉ ጽፈዋል

ዮርዳኖስ የተባለች አስተያየት ሰጪም "ኦባማ ስለ ሰላም ሊናገር ሄዶ፣ በሰላም አዳራሽ ውስጥ የጦርነትን አስፈላጊነት ተናግሮ ወጥቷል። ሰላም ሰላም ስለተባለ ብቻ ሰላም አይመጣም። ሰላምን ለማምጣት ሀይል የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ሂትለር በሀይል ባይወርድ ኖሮ ያሁኑዋ ሰላማዊት እና ዴሞክራሲያዊት ጀርመን/አውሮፓ ባልተወለደች ነበር። በአገራችንም የሚያስፈልገው ይህ ነው። በሰላማዊ ትግል ስለታገሉ ብቻ ሰላም ይመጣል ማለት ሞኝነትና አላዋቂነት ነው። ኦባማ ታሪክን አገላብጡ ያለንም ለዚሁ ነው። ታሪክ ደግሞ ሁሌም በጦርነትና በሰላም የተሞላ ነው" ስትል ተናግራለች።

## የነፍሰ ገዳዩና ዘረኛው መለስ ዜናዊ በኮፔን ሃገኑ .. ከገጽ 1 የዞር

እንደሪፖርተራችን ዘገባ ሰላማዊ ሠልፈኞቹ ተቃውሞአቸውን ለማሰማት ከተለያዩ የአውሮጳ አገሮች በየብስ፤ በባህርና በአየር ረዥም ርቀት ተጉዘው የመጡ መሆናቸው ሲታወቅ ለበርካታ ወገኖቻችን በጠራራ ጸሃይ በአጋዚ ጦር መጨፍጨፍ፤ መታሰርና ከአገር መሰደድ ምክንያት የሆነው ይህ ከዘመናችን ጨካኝ አምባገነኖች የመጨረሻው ደረጃ ላይ የሚገኝ ኋላ ቀር ሰው አፍሪካን ወክሎ እንዲገኝ መደረጉ እጅግ አበሳጭቶአቸው እንደሆነ ያነጋገራቸው ሰልፈኞች ገልጸዋል;፡

አዲስ አበባ የሚገኙት ምንጮቻችን እንዳረጋገጡት መለስ ዜናዊ በዚህ ጉባኤ ላይ አፍሪካን ወክሎ ለመገኘት የቻለው በጸረ ዲሞክራሲያዊነቱና በሰብአዊ መብት ጥሰት ሪኮርዱ ምክንያት የተበላሸውን አለም አቀፍ ገጽታውን ለማሻሻል እንዲችል መድረክ ለማግኘት በአዲስ አበባ የሚገኙትን ትላልቅ የአፍሪካ አገራት አምባሳደሮችን በማግባባት፤ መደለያ በመስጠትና በመለማመጥ የየአገሮቹን ድጋፍ ለማሰባሰብ ከቻለ ቦኋላ ነው።

የመለስ ዜናዊን በኮፐንሃገን ግባኤ ላይ መገኘት ለመቃወም በዛሬው ቀን የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በነገውም ዕለት እንደሚቀጥል የታወቀ ሲሆን በዛሬው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የአውሮፓ ፓርላማ አባላትም ከኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን መለስ ዜናዊ በሃገሪቱ ሕዝብ ላይ እየፈጸማ ያለውን በደል በማጋለጥ ለፈጸማቸውም በደል በህግ እንዲጠየቅ ጥሪ እያቀረቡ መሆናቸው ተዘግቦአል።

ይህ በንዲህ እንዳለ መለስ ዜናዊ የተላከበትን አላማ በጥቅም በመሸጥ የአፍሪካን ጥቅም አሳልፎ ሰጥቷል ሲል ጃሚ ሄን የተባለው የዴንማርክ ጋዜጠኛ አጋለጠ። ጋዜጠኛ ጃሚ ሄን "Corruption: Sarkozy, Obama Pressure Ethiopia's Zenawi to Betray Africa's Future at Copenhagen Climate Talks" በሚል ርዕስ በኢንተርኔት ለመላው አለም ባሰራጨው ዘገባው በፈረንሳዩ መሪ በሳርኮዚና አፍሪካን በመወከል የመጣው መለስ በፓሪስ ላይ የደረጉት የሁለትዮሽ ስምምነት በኮፐንሃገን የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ አበብሶታል ብሏል።

መለስ የአፍሪካን ጉዳይ እዚያው በኮፐንሃገን ጉባኤ መፈጸም ሲገባው የራሱን ድብቅ ፍላጎት ለማሳካት እግረመንገዱን ፈረንሳይና እንግሊዝ የተጓዘ ሲሆን ከፕ/ት አኦባማም ጋር በስልክ መወያየቱን ለማወቅ ተችሏል። መለስ ከሶስቱ ሃያላን መንግስታት መሪዎች ጋር ባደረገው ውይይትም የአፍሪካን ጥቅም የማያስጠብቅ ስምምነት ላይ መድረሱን በኢንተርኔት የተሰራጨው ዘገባ በይፋ አጋልጦታል።

የመለስ የተናጥል ስምምነት በኒኮላስ ሳርኮዚ ድረ-ገጽ ላይ የወጣ ሲሆን ይህንን የተመለከቱ የፓን አፍሪካ ንቅናቄ አቀንቃኞችና በ 10 ሺዎች የሚቆጠሩ በኮፐንሃገን የተሰበሰቡ ሰላማዊ ሰልፈኞች ቁጣቸውን በእጅጉ እያሰሙ መሆናቸውን ጸሃፊው ገልጿል።

ግንቦት 7 እና 18 ልዩ-ልዩ ተቋማትን ያካተተው አድቮካሲ ኢትዮጵያ በመባል የሚታወቀው ድርጅት ባለፈው ሳምንት በየግላቸው ለአለም መንግስታት በላኩት መልዕክት መለስ ዜናዊ አፍሪካን የመወከል የሞራልም የህግም ስልጣን እንደሌለው በመግለጽ በሃገሪቱ የዜጎችን ሰባዊ መብት ከመጣስ አልፎ ደኖችን በማጥፋትና ወንዞችን በመበከል እየፈጸመ ያለውን በደል በዝርዝር አስቀምጧል።

## መለስ ዜናዊ የአሜሪካ አምባሳደርን "ደደብ " ሲል .. ከገጽ 1 የዞር

የህዝባቸውን ስሜትና ድምጽ ለመስማት የማይፈልጉ አምባገነኖች ሁሉ በተባበረ የህዝብ ትግል ወደማይቀረው የስልጣን ዘመናቸው ፍጻሜ ሲቃረቡ ስድብን ፤ የህዝብ ንቀትንና የቀድሞ ወዳጆቻቸው የሆኑትን ምዕራባዊያን ማብጠልጠል የተለመደ ተግባር እንደሆነ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ታይቶአል ። ሳዳም ሁሴን፣ መንግሥቱ ሃይለማሪያምና የሰሞኑ የመለስ ዜናዊም ጋጠወጥ ድርጊቶች የዚሁ ክስተት አብይ ማስረጃ አካል ናቸውም ተብሎአል።

ይህ በዚህ እንዳአለ "አንዳንድ ፓርተቲዎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ችግር ለመፍታት በኬንያና በዚምባቡዌ እንደ ታዬው አይነት የጋራ መንግሰት መመስረት አማራጭ መሆኑን ይናገራሉና መንግስትዎ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አለው" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስም "የኬንያና የዚምባብዌ ሞዴል የቀለም አብዮት የቅርብ ጊዜ ሞዴል ሲሆን በምርጫ በሚፈጠር ብጥብጥ መንግስትን ለማስወገድ የሚታለም ነው። ይህም ካልተቻለ ደግሞ መጀመሪያ ስልጣን በመጋራት በሂደት ከስልጣን ማስወገደን አላማ ያደረገ ነው" ካለ ቦኋላ "እንዲህ አይነት ነገር በኢትዮጵያ ሊሞከር አይችልም ባይባልም ይህን የሚያደርጉ ሰዎች ኢህአዴግ ስህተትን እንደማይደግም በጸረ ደርግ ትግል የወሰዳቸውን እርምጃዎች የማይገነዘቡና በምርጫ 97 የተከሰተውን አይነት ስህተት ላለመድገም እያተደረገ ያለውን ዝግጅት ለመረዳት የማይችሉ ናቸው" በማለት ማስጠንቀቂያ አዘል መልስ ሰጥቶአል። በመቀጠልም የዚህ አይነት ሁኔታ እንዳይፈጠር ኢህአዴግ አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀቱን በማያሻማ ቋንቋ አስጠንቅቆአል። ይህን የመለስ ቃለመጠይቅ ከተከታተሉ የፖለቲካ ተንታኞች አስተያየት እንደተደመጠው የመለስ ንግግር በሰላማዊ ትግል ስትራቴጂ ወያኔ ላይ ጫና ፈጥረን ከተቻለ በመጪው ምርጫ 2002 የጋራ መንግሥት ለመመስረት የሚያስችል ድምጽ ማግኘት እና በሂደት ምርጫውን የበለጠ ግልጽና ነጻ በማድረግ ወደ ዲሞክራሲ ሥርዓት እንሄዳለን የሚሉትን ተቃዋሚዎች ለማስጠንቀቅ የታለመ እንደሆነ ተናግረዋል።

በያዘው መሳሪያ ብዛትና አለኝ ብሎ በሚመጻደቀበት ጉልበት የሚስተካከለው እንደሌለ ለማመላከትም"**ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች**" በማለት እንደተረተባቸው ተደምጦአል።

በመቀጠልም መለስ በዚህ እርቃኑን ባሰቀረው ቃለ መጠይቁ ተቃዋሚወች ሁሉ ከወይዘሪት ብርቱካን እንዴት መማር እንዳለባቸው ሲናገር አንድ ወር ሙሉ አቋሟን ለማስቀየር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተደረገው ጥረት ምንም ፍሬ ስላላፈራ አሁን ያለችበትን መመልከቱ በቂ ነው ሲል ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ሊያፈነግጥ የሚሻ ሰላማዊ ታጋይ ነኝ የሚል ድርጅትና ግለሰብ ዕጣ ምን ሊሆን እንደሚችል አመላክቶአል።

በቅርቡ በተፈረመው የሥነ-ምግባር መመሪያ ተብዬ ሰነድ በወያኔ እስር ቤት ውስጥ ያሉ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ ስምምነት ተደርጎአል ተብሎ ስምምነቱን በፈረሙት ፓርቲዎችና ደጋፊዎቻቸው የሚናፈሰው ዜና ፍጹም እንደማያውቀው የተናገረው መለስ ዜናዊ የስምምነቱ እርዕሰት ምርጫ 97ን ተከትሎ በተፈጠረው ሁኔታ ታሰረው ያልተፈቱ ካለ እነርሱን የሚመለከት ነው በማለት አስተያየቱን አጣጥሏል ።

## ወያኔ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ለማስመረጥ .. ከገጽ 1 የዞር

ሌላው አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው የትናንቱ የአስመራጮች እና የታዛቢዎች ምርጫ የደርግን የምርጫ ጊዜ ያስታውሰኛል ያሉ ሲሆን ፣ በሀያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን አገራችን አሁንም በኮሚኒስት ህግ መተዳደሩዋ በእጅጉ ያበግነኛል ብለዋል። እኛ የምናውቃቸው የወያኔ ደጋፊዎች እርስ በርሳቸው ሲመራረጡ እየተመለከትን ነጻ ምርጫ የምንጠብቅ ከሆነ እጅግ ሞኞች ነን ያሉት እኚህ አስተያየት ሰጪ፣ ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ አገራችን በምርጫ የመንግስት ለውጥ ታመጣለች ብየ ቅንጣት ታክል አላስብም ብለዋል።

አቶ ወርቁ መጃ የተባሉት አስተያየት ሰጪም የሌሎችን አስተያየቶች ያጠናከሩ ሲሆን፣ ተገደውና ማስፈራሪያ ደርሶአቸው ወደ አዳራሹ ቢሄዱም በአዳራሹ ውስጥ ሲሰራ የነበረው ተንኮል ሁሉ ጨዋራቸውን ሲልጠው እንደነበር ሳይሸሽጉ ተናግረዋል።

አንድ ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገ በሀያዎቹ የ እድሜ ክልል የሚገኝ ወጣት በበኩሉ "ይብላኝ ለተቃዋሚዎች አሁንም ነጻ ምርጫ ይኖራል ብለው ለሚያስቡት፣ እኛስ ድሮውንም እርማችንን አውጥተናል። ዛሬም የተገኘሁት ወሬ ልለቅም ነው እንጅ እውነተኛ ምርጫ ይኖራል ብየ አይደለም። ነጻ ምርጫ ቴሌቪዥን ውስጥ ቀረ። አሁንማ ነጻ ምርጫ የሚያካሂዱ አገሮችን እየሰማን እንዳንበሳጭና መንግስታችንም እንዳይበሳጭ ነው መሰለኝ፣ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ስለሚያደርጉ አገሮች የወያኔው ሚዲያዎች መዘገብ አቁመዋል " ብሎአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ9610 KHZ በ31 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org